# መግቢያ

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በሕግ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት ከ1934 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ከወጡት ሕጎች መካከል በስራ ላይ ያሉትን ለይቶ በ28 ክፍሎች እና በሰባት ቅጾች አጠቃልሎ አዘጋጅቷል፡፡ ይህን ስራ አጠናቅቆ ወደ ስራ ለማስገባት በቢ.ፒ.አር 72 ወራት እንዲሁም ለስራው በተቀረጸ የስራ ዕቅድ 21 ወራት የተያዘ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ህጉ ከፍተኛ አመራር በሰጠው ከፍተኛ የስራ አመራር እና የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት ባደረጉት ከፍተኛ ርብርብ ከ12 ወር በታች በፈጀ ጊዜ ውስጥ ህጎቹን አጠቃልሎ ለማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት ሕጎችን ለማጠቃለል ሙከራ የተደረገ ቢሆንም የቀደማዊ ኃይለስላሴ ዩንቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ 1965 ዓ/ም የተጠቃለሉ ሕጎችን ካሳተመ ወዲህ የአገሪቱ ሕጎች ሳይጠቃለሉ ላለፉት 43 ዓመታት ቆይተዋል፡፡ ሕጎችን የማጠቃለል ስራ በአሁን በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በተተካው በቀድሞው የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር በ1995 ዓ/ም ተጀምሮ እስከ 1998 ዓ/ም ድረስ ሲሰራ የቆየ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ሊቋረጥ ተገዶ የነበረ ሲሆን ከዚሁ የማጠቃለል ስራ ህትመት በኋላ አገራችን በሶስት የተለያዩ የመንግስት የአስተዳደር ስርዓት አማካኝነት በርካታ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦችን አስተናግዳለች፡፡ እነዚህን ለውጦች ተከትሎም በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት፣ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት፣ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የተለያዩ ሕጎች ወጥተዋል፡፡

እነኚህ ሕጎች የሚሸፍኗቸው ጉዳዮች በርካታ በመሆናቸው ከህጎች የተደራሽነት ችግር ጋር ተዳምሮ ተጠቃሚዎች የተሻረውንና በሥራ ላይ ያለውን ሕግ በቀላሉ ለመለየት የማይችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በመሆኑም ይህን ችግር ለመፍታት የሀገሪቷን ህጎች አጠቃልሎና አቀናብሮ በማዘጋጀት ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ የሚጫወተው ሚና የማይተካ ነው፡፡

ዳኞች፣ ዐቃብያነ ህግ፣ ጠበቆች፣ የህግ አማካሪዎች፣ ነገረ ፈሪዎች፣ የወንጀል ምርመራ ፖሊስ አባላት እና ሌሎች የፍትህ አስተዳደሩ ተዋንያን በህግ የተሰጣቸውና ኃላፊነትና ሙያዊ ግዴታ በሚወጡበት ጊዜ በስራ ላይ ያሉ ህጎች ከተሻሩ ወይም ከአገልግሎት ውጪ ከሆኑ ህጎች በመለየት በተሻሩ ህጎች ላይ ተመርኩዘው ከሚደረጉ ክርክሮችና ከሚሰጡ



www.chilot.me

ውሳኔዎች የራቀ የፍትህ ስርዓትን ለመገንባት ለሚደረገው ጥረትም የህግ ማጠቃለል ስራው ጉልህ ሚናን ያበረክታል፡፡

ህጎች የመንግስትን ስልጣን የሚወስኑ በመሆኑ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ከተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር አንጻር ህጋዊ መሰረት ያለው የህዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ እና የአሰራር ግልጸኝነት እና ተጠያቂነት እንዲጎለብት ህጎችን ማጠቃለል እና ተደራሽነቱን ማስፋት አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

የወጪ ኢንቨስትመንትንም በተመለከተ ህጎች በአንድ ሰነድ ተጠቃልለው መገኘት መቻላቸው በሀገሪቷ ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካ ሁኔታ እንዲሁም የፍትህ ስርዓቱን ባህሪያትና የህግ ጥበቃ (ክልከላ) በሚገባ ለማወቅ የሚረዳ በመሆኑ ኢንቨስትመንትን በማበረታታቱ ረገድ የጎላ ጥቅም አለው፡፡

እንዲሁም በቀጣይ ፌዴራል ጠቅላይ ፀ/ህጉ ለመስራት ላቀደው ተቀራራቢ ባህርይ ያላቸውና ተበታትነው ለየብቻቸው ያሉ ሕጎችን አሰባስቦ የተዋሃደ ሕግ /ኮድ/ የማዘጋጀት ስራ ጠቃሚ መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

ሕጎችን ለማጠቃለል የሚቻለው ሀገሪቷ በህግ አወጣጥ የረጅም ጊዜ ታሪኳ በነጋሪት ጋዜጣ አትማ ያወጣቻቸውን ህጎች በተሟላ ደረጃ አሰባስቦና አሟልቶ መያዝ ሲቻል ነው፡፡ በዚህ ረገድ የቀድሞ ፍትህ ሚኒስቴር በአስራ አንድ ቅጽ ያሰባሰበውና ከ1934 ዓ/ም እስከ 1987 ዓ/ም ባለው ጊዜ የወጡትን ሕጎች የያዘው ስብስብ ለሥራው ቅልጥፍና ከፍተኛ እገዛ አድርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከ1987 ዓ/ም ወዲህ የወጡ ሕጎችን ከብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤት ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ባለፈ የስራውን ጥራት ለማስጠበቅ እና ግድፈቶች እንዳይፈጠሩ የ1965 ዓ/ምህረቱን የተጠቃለሉ ህጎች እና በአቶ አብደላ አሊ ተዘጋጅተው ስራ ላይ የዋሉ ሁለት የህግ ማመላከቻዎችን (directories) በአጋዥነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ስራውን ውጤታማ ከማድረግ አንጻር አሳሳቢ ሆኖ የነበረው ተግዳሮት ሁሉንም የሚጠቃለሉ ህጎችን በወርድ ፎርማት ማግኘት ያለመቻል ሲሆን ይህ ችግር በሌላ መንገድ መፍትሄ ካላገኘ በስተቀር ከ5400 ገጽ በላይ የሆኑትን ህጎች በእጅ ጽሁፍ ጽፎ ለማጠናቀቅ



www.chilot.me

ከሚወስደው ጊዜ እና ከሚያስፈልገው የሰው ሀብት አንጻር በታቀደለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ይህንኑ በመገንዘብ ከሳይንስ እና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል ጋር መልካም የስራ ግንኙነት በመፍጠር በፒዲ ኤፍ ፎርማት ተይዘው የነበሩ ህጎችን ወደ ቴክስት ወይም ወርድ ለመቀየር የሚያስችል የአይ ሲ ቲ ዘዴ በመፍጠር እና ሰነዶቹን ለውጠው በማስረከብ ከፍተኛ የስራ ትብብር አግኝተናል፡፡ ይሁንና ዘዴው መቶ በመቶ ህጎቹን በነበሩበት ሁኔታ መለወጥ ያልቻለ እና የተወሰኑ ቃላትን፣ ቁጥሮችን፣ ሳጥኖችን እና ምልክቶችን ባልተገባ የሚለውጥ በመሆኑ እንኚህን ግድፈቶች ማስተካከሉ እና ማረሙ ፈታኝ እና ተጨማሪ የሰው ሀይል የፈለገ ሆኖ በመገኘቱ ተጨማሪ ባለሙያ እንዲካተት በማድረግ ስራውን በፍጥነት ለመጨረስ ተገቢው ጥረት ተደርጓል፡፡ እነኚህም ባለሙያዎች የታረሙትን ህጎች በጥራዝ መልክ ከተያዙ ህጎች ጋር በማመሳሰል የማጥራት ስራውን ሰርተዋል፡፡

በዚህ ሕጎችን የማጠቃለል ስራ ውስጥ ሌላው አስቸጋሪውና ጥንቃቄ የጠየቀው ሥራ በግልጽ ሳይነገር የተሻሩትን እና ከሥራ ውጭ የሆኑትን ሕጎች የመለየቱ ሥራ ነው፡፡ ይህ ስራ አግባብነት ያላቸውንና በስራ ላይ ያሉትን ሕጎች እያንዳንዱ አንቀጽ ማንበብ ጠይቋል፡፡ በመሆኑም ሥራው የኮሚቴውንና የኮሚቴውን አባላት ሰፊ ጊዜ ወስዷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኮሚቴው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች የሚጠቀሙባቸውንና በስራ ላይ ያሉ ሕጎችን ዝርዝርም እንዲልኩ አድርጓል፡፡ ይህ የተደረገው በሚገባ ሳይታይ የሚታለፍ ሕግ እንዳይኖር በማሰብ ነው፡፡

አገራችን ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ የምትከተለው የአስተዳደር ዘይቤ ፌዴራላዊ የመንግስት አስተዳደር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 52ም የፌዴራሉ መንግስት ሕግ ሊያወጣባቸው የሚችልባቸውን ጉዳዮች ለይቶ ደንግጓል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ያጠቃለለውም ህግ ከነሐሴ 1987 በፊት ወጥተው ክልላዊ ባህሪይ የሌላቸውንና ከነሐሴ 1987 ዓ/ም ወዲህ ሥልጣን ባላቸው የፌዴራል መንግስቱ አካላት የወጡትን ሕጎች ብቻ ሲሆን ከላይ ከተገለጸው የህገመንስቱ ድንጋጌ አንቀጽ 52 ላይ ከተደነገጉት ጉዳዮች ውጭ ባሉ ጉዳዮች ላይ የክልል ብሔራዊ መንግስታት ሕግ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡ እነኚህ በክልላዊ መንግስታት የወጡ ህጎች በህግ ማጠቃለል ስራው ውስጥ አልተካተቱም፡፡



www.chilot.me

በስተመጨረሻም በዚህ የህግ ማጠቃለል ስራ ላይ ለተሳተፉት የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት እና የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልን በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ኤምባሲ ከፍ ያለ ምስጋናዬን እያቀረብኩ በስራው ላይ በማረም፣ መረጃ በማቀበል፣ በጽሁፍ ስራ፣ ሰነዶችን ከፒ.ዲ.ኤፍ ወደ ቴክስት በመቀየር፤ ህጎችን፣ ማገኛችን፣ ሰንጠረገሮችን እና ምልክቶችን በመስጠት እና ማናቸውንም ሌላ አይነት እገዛ በማድረግ ከጎናችን ለነበራችሁ ግለሰቦች እና ተቋማት ከፍ ያለ ምስጋናዬን እያቀረብኩ ስራው በበለጠ ያለቀለት እና ከእንከን የጸዳ ይሆን ዘንድ የሚኖራችሁን ማናቸውንም አይነት አስተያየት ለማጠቃለል ስራው የቴክኒክ ኮሚቴው መስጠት የምትችሉ መሆኑን እገልጻለው፡፡

ጌታቸው አምባዬ

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

የካቲት/2009 ዓ/ም

አዲስ አበባ



www.chilot.me

## ህጎችን ማጠቃለል

### 1. ትርጉምና አስፈላጊነት

ሕጎችን ማጠቃለል ማለት ያልተሻሩትን ሕጎች ከተሻሩት ሕጎች ለይቶ በስራ ላይ ያለውን ሕግ ለተጠቃሚው በሚያመች መልክ አሰናድቶና አቀናብሮ ማቅረብ ማለት ነው፡፡ አንድ ሕግ በግልጽ ሊሻር፣ በግልጽ ሳይነገር ሊሻር ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው በመሆኑ አገልግሎቱን ሲፈጸም ከስራ ውጭ ሲሆን ወይም በጊዜ ብዛት ወይም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በመለወጣቸው ምክንያት ከሥራ ውጭ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ሕግ አልተሻረም ለማለት ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ከአራቱ መንገዶች በአንዳቸውም ቢሆን ከሥራ ውጪ አልተደረገም ማለት ነው፡፡

ሕጎችን ማጠቃለል ሕጎችን ከማሰባሰብ እና ሕጎችን በኮድ (በተዋሃደ ሕግ) መልክ ከማዘጋጀት ይለያል፡፡ ሕጎችን ማሰባሰብ ህጎቹ የወጡበትን ዘመን ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ ወይም አግባብነት ያለውን የርዕስ አከፋፈል ዘዴ በመጠቀም ሕጎችን ለተጠቃሚው ማቅረብ ነው፡፡

በህጎች መሰባሰብ ውስጥ ሻሪና አሻሻይ ሕጎች ሊገለጹ የሚችሉ ቢሆንም በተጠቃለሉ ሕጎች ዝግጅት ልክ ያልተሻረው ሕግ ከተሻረው ሕግ ተለይቶ በተቀናበረ ሁኔታ የሚዘጋጁ ሰነድ አይኖርም፡፡

ተመሳሳይ ባህሪይ ያላቸውን በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን በአንድ ላይ አዋህዶ ኮድ ማዘጋጀትም ሕጎችን ከማጠቃለል ይለያል፡፡ ሕጎች ኮዲፋይ ሲደረጉ (ሲዋሃዱ) ነባር ሕጎች ተሽረው በተዋሃደው ሕግ (ኮድ) ይተካሉ ሕጎችን ማጠቃለል በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን በተቀናበረ ሁኔታ ተጠቃሚ ከማቅረብ ባለፈ ሥራው የህጎችን መሻር አያስከትልም፡፡



www.chilot.me

በአገራችን ሕጎች ተደራሽ የሚሆኑበት ዘዴ /መንገድ/ወሰን መሆኑን የዘዴውም ውጤታማ አለመሆኑን እና የሕጎች መብዛት ሕጎችን የማጠቃለል ሥራን ግዴታ ያደርጉታል፡፡

ሕጎች ተጠቃልለው የማይገኙ በመሆኑ ከሕግ ሙያ ውጭ ያሉ ሰዎችም ሆኑ የሕግ ባለሙያዎች በሥራ ላይ ያሉትን ሕጎች በቀላሉ እና በእርግጠኝነት ለመለየት ፈታኝ ነው፡፡ የተሻረውና ያልተሻረው ሕግ ተለይቶ በተቀናበረ (systematic) ሁኔታ የተዘጋጀ ሰነድ ባለመኖሩ በተሻረ ሕግ የመስራት ወይም ምክር የመስጠት አደጋ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ሕጎችን ማጠቃለል ይህንን መሠረታዊ ችግር የመቅረፍ አቅም አለው፡፡

በዚህ አግባብ ያልተሻሩ አዋጆች እና ደንቦች ሁሉ በዚህ የህጎች ማጠቃለል ስራ ውስጥ ተካትተዋል፡፡ ሕጉ በሥራ ላይ ያለ ሕግ ሆኖ የሕጉ የተወሰነ ክፍል ብቻ በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በግልጽ ሳይነገር የተሻረ ወይም የተሻሻለ ከሆነ የሻረው ወይም የአሻሻዩ ሕግ አንቅጽ አግባብነት ያላቸውን የዋናውን ህግ (የእናት ሕጉን) አንቅጽ እየተኩ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ይህው ስለመሆኑም በእያንዳንዱ ለውጦች የግርጌ ማስታወሻ በማስቀመጥ ለተጠቃሚው በሚያመች መልኩ አንድ ሰነድ ሆኖ ተዘጋጅተዋል፡፡

ለምሳሌ ፡ የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 (2/13) በአዋጅ ቁጥር 138/1991 ፣ በአዋጅ ቁጥር 254/1993፣ በአዋጅ ቁጥር 321/1995፣ በአዋጅ ቁጥር 847/2006 እና በአዋጅ ቁጥር 454/1997 ተሻሽሏል፡፡ አዋጅ ቁጥር 25/1988 መሻሻል አለመሻሻሉን ለማወቅ የሚፈልግ ተጠቃሚ አምስቱንም አሻሻይ ሕጎች ማየት ይኖርበታል፡፡

ሆኖም ሕጉ ሲጠቃለል የተሻሪዎቹ ነባር አንቅጾች ወጥተው የአሻሻዮች ወይም የሻሪዎች ሕጎች አዳዲስ አንቀጽ በቦታቸው ተተክተውና ተሳትረው ሕጉ አንድ ሰነድ ሆኖ ተዘጋጅቶ ያገኛዋል፡፡ ስለ ተኪዎቹ አንቀጾች፣ ንዑሳን አንቀጾች እና ቅጽ የግርጌ ማስታወሻ ተዘጋጅተዋል፡፡ ከእናት ህጉ ውስጥ የተሰረዘ አንቀጽ ወይም ንዑስ አንቀጽ ያለ እንደሆነና ይህ አንቀጽ ወይም ንዑስ አንቀጽ በአዲስ ያልተተካ



www.chilot.me

እንደሆነ ነበሩ አንቀጽ ወይም ንዑስ አንቀጽ እንዲወጣ ተደርጎ ባዶውን ከተተወ በኋላ የወጣበት ምክንያት በግርጌ ማስታወሻ ይገለጻል፡፡

የውጭ ኢንቨስተሮች ወይም አማካሪዎቻቸው በአገሪቱ ውስጥ በስራ ላይ ያሉት የፌዴራል ሕጎች ምንድን ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ግልጽ መልስ ያገኛሉ፡፡ የፍትህ አስተዳደሩም በስራ ላይ ያሉት ሕጎች ተቀናብረው በአንድ ሰነድ ከመቅረባቸው ዋነኛ ተጠቃሚ ነው፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 6 (5) (ለ) መሰረት ሕጎችን የማጠቃለል ሥራ እንዲሰራ በህግ ሥልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሲሆን መስርያ ቤቱ በዚሁ ስልጣኑ መሰረት ህጎቹን በዚህ መልኩ ማጠቃለሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀጣይ በህግ አውጪው የመንግስት አካል በየጊዜው የሚወጡ አዳዲስ ሕጎችንና አሻሻይ ህጎችን እየተከታተለ የተጠቃለሉን ሕጎች ወቅታዊነት በማስጠበቅ (updating) ሳይቆራረጥ የተደራሽነትን ችግር በመሰረታዊነት የሚፈታ ይሆናል፡፡

## 2. <u>በግልጽ የተሻሩ ህጎች</u>

በዚህ የህግ ማጠቃለል ስራ ውስጥ ቀላሉ ስራ በግልጽ የተሻሩ ሕጎችን የመለየቱ ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም ህጎቹ በመጨረሻ ክፍላቸው የሻሯቸውን ህጎች በግልጽ በመጥቀስ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ህጎችን በቀላሉ የሚለዩልን በመሆኑ ነው፡፡ እነኚ ህጎች ከተሻሩበት ጊዜ ጀምሮ አይሰራባቸውም፡፡ በዚህም መሰረት በዚህ አግባብ በግልጽ የተሻሩት ሕጎች በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ እንዲገቡ አልተደረገም፡፡

## 3. <u>ማሻሻያዎች እና መሻሪያ ሕጎች</u>

የአንድ ሕግ አንቀጽ ወይም ንዑስ አንቀጽ ቀድሞ የወጣን ዋና (እናት) ሕግ ያሻሻሉ እንደሆነ የእናት ሕጉ ተሻሻይ አንቀጽ ወይም ንዑስ አንቀጽ ወጥቶ በአዲሱ አንቀጽ ወይም ንዑስ አንቀጽ እንዲተካ ተደርጓል፡፡

በማሻሻያው ሕግ የተሻረ አንቀጽ ወይም ንዑስ አንቀጽ ሲኖር ይኸው የእናት ሕጉ የተሻረው አንቀጽ ወይም ንዑስ አንቀጽ ከተጠቃለለው ሕግ ውስጥ እንዲወጣ



www.chilot.me

ተደርጓል፡፡ የእናት ሕጉ የተወሰነ ክፍል የተሻሻለበትን ወይም የተሻረበትን አግባብ ለማብራራት የተሻሻሉ ወይም የተሻሩ አንቀጽ ባሉበት ገጽ ሁሉ የግርጌ ማስታወሻ ተዘጋጅቷል፡፡

በመሆኑም የህጎችን የመሻርም ሆነ የመሻሻል ሁኔታ በተመለከተ በእያንዳንዱ ህግ ውስጥ በግርጌ ማስታወሻ የተገለጹትን ማመላከቻዎች በሚገባ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ አንድ አሻሻይ ህግ የእናት አዋጁን አንቀጽ ወይም ንዑስ አንቀጽ ሽሮ እንደሆነ በዚህ የህግ ማጠቃለል ስራ ውስጥ ከአንቀጹ ወይም ከንዑስ አንቀጹ ቁጥር ውጪ የአንቀጹ ድንጋጌ ሙሉ በሙሉ እንዲወጣ ወይም ባዶ እንዲሆን ከተደረገ በኋል ድንጋጌው የወጣበት ምክንያት በግርጌ ማስታወሻ ይገለጻል፡፡

## 4. <u>በግልጽ ሳይነገር የተሻሻሉና የተሻሩ ሕጎች</u>

ቀድሞ በወጣ ሕግ በተሸፈኑ ጉዳዮች /Subject Matter/ ላይ ሌላ ሕግ የወጣ እንደሆነ በጊዜ ሂደት በኋላ የወጣው ሕግ ቀድሞ የወጣውን ሕግ ይሽራል በሚለው መሠረታዊ የህግ አተረጓጎም መርህ መሠረት የቀድሞ ሕግ ወይም የተወሰኑ የሕጉ ክፍሎች በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በኋላ በወጣው ሕግ በግልጽ ሳይነገር ሊሻሩ ወይም ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡

በዚሁ አግባብ ቀድሞ በሌላ ሕግ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የወጡ ሕጎች የሻሯቸውን ወይም ያሻሻሏቸው ነባር አናቅጽ እንዲወጡና በአዳዲሶቹ አንቀፆች እንዲተኩ ተደርጓል፡፡ ከዚህም የተነሳ ሻሪዎች ወይም አሻሻዮች አንቀጽ ባሉበት ገጽ ሁሉ የግርጌ ማስታወሻ ተዘጋጅቷል፡፡ የግርጌ ማስታወሻውም አንቀጽ በግልጽ ሳይነገር ተሽረዋል ወይም ተሻሽለዋል የተባለበትን ምክንያት ያብራራል፡፡ በህግ ማጠቃለል ስራው ከባዱ እና ከፍተኛ ጥናታቂ የሚፈልገው ስራ በግልጽ ሳይነገሩ የተሻሩ ህጎችን የመለየት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንቱም የእናት ህጉ ድንጋጌዎች መሻር ያለመሻራቸውን በእርግጠኝነት ለማወቅ ከጉዳዩ ጋር የሚቀራረብ ባህሪ ያላቸውን ህጎች ሁሉ የመፈተሽ እና የእነዚህ ህጎች ድንጋጌዎች የእናት ህጉን ድንጋጌዎች ጉዳዮች (subject matter) መሸፈን አለመሸፈኑን ወይም መሻር አለመሻሩን ለማወቅ ቀላል አይሆንም፡፡



www.chilot.me

## 5. ከሥራ ውጭ የሆኑ ሕጎች

አንዳንድ ሕጎች ነባራዊው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በመለወጣቸው ከሥራ ውጭ ይሆናሉ፡፡ አንዳንድ ሕጎች ደግሞ የተደነገጉበትን አላማ ያሳኩና የፈጸሙ በመሆናቸው ወይም ሕጎቹ እንዲያገለግሉ የተወሰነላቸው ከፍለ-ጊዜ ያበቃ በመሆኑ ከሥራ ውጭ ይሆናሉ፡፡

በዚህ ሁኔታ ከሥራ ውጭ የሆኑ ሕጎች በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ እንዲካተቱ አልተደረገም፡፡ ከሥራ ውጭ በመሆናቸው በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ እንዳይገቡ የተደረጉት ሕጎችን ጨምሮ በሀገሪቷ ዘመናዊ የህግ አወጣጥ ታሪክ ውስጥ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው ወጥተው የነበሩ ህጎች ዝርዝር እና አጭር ማብራሪያ በተጠቃለሉ ሕጎች ቅጽ 7 መጨረሻ ላይ ተዘጋጅቷል፡፡ ምንም እንኳን አብዛኞዎቹ ህጎች የተሻሩ እና ከጥቅም ውጪ የሆኑ ቢሆንም ለምርምር እና ጥናት አላማ እንዲሁም ሀገሪቷ ቀድሞ የነበሯት ህጎች አሁን ካለው የህግ አወጣጥ እድገት ጋር ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ለማነጻጸር ይረዳሉ፡፡

## 6. ኮዶች

በመጽሀፍ ተጠርዘው የወጡት ኮዶች ማለትም የፍትሐ ብሔር ሕግ፣ የወንጀል ሕግ፣የንግድ ሕግ፣ የቤተሰብ ሕግ፣ የባህር ህግ፣ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግና ወንጀል መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ተቀናብረው የሚገኙ በመሆናቸው በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ እንዲካተቱ አልተደረገም፡፡ እነኚህን ኮዶች በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ ማስገባቱ የተጠቃለሉ ህጎችን ከማብዛት ያለፈ ጥቅም አይኖረውም፡፡

ሆኖም ኮዶቹ የታወጁባቸው ሕጎች የኮዶቹን የተወሰኑ አንቀጾ የሻሩ ወይም ያሻሻሉ ሕጎች፣ ዝርዝር ከማብራሪያ ጋር በተጠቃለሉ ሕጎች በቅጽ 7 መጨረሻ ላይ ቀርቧል፡፡

## 7. አለም አቀፍ ስምምነት ማጽደቂያ፣ የበጀት ሕጎችና የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብ

አለም አቀፍ ስምምነት ሲጸድቅ ማጽደቂያ አዋጁ እንጂ የስምምነቱ ዝርዝር በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የማይወጣ በመሆኑ ማጽደቂያ ሕጎች በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ አልተካተቱም፡፡

የበጀት ማጽደቂያ አዋጆችም የአገልግሎቱ ዘመናቸው ለሰጡበት ዘመን ብቻ በመሆኑ በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ እንዲካተቱ አልተደረገም፣ በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብ ቁጥር 122/1985 አማካይነት የኢትዮጵያ ሕግ አካል የተደረገው የጉምሩክ ስምምነትም በነጋሪት ጋዜጣ ስላልታተመ በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ አልተካተቱም፡፡

ሆኖም የአለም አቀፍ ስምምነት ማጽደቂያ ሕጎች፣ የበጀት አዋጆች እና ደንብ ቁጥር 122/1985 ከነማሻሻያዎቻቸው በተጠቃለሉ ሕጎች ቅጽ 7 ላይ ተዘርዝረዋል፡፡

## 8. በሥራ ላይ ያሉ /ያልተሻሩ/ ሕጎችን ስለ ማግኘት

ተጠቃሚው ከተጠቃለሉት ሕጎች ውስጥ የሚፈልገውን ሕግ በቀላሉ ማግኘት እንዲችል የሕጎችን ባህሪይ መሠረት በማድረግ ሕጎቹ በክፍልና በንዑስ ክፍሎች ተካፋፍለዋል፡፡

የክፍሎ የንዑሳን ክፍሎቹ ክፍፍል መሠረት ያደረገው የሕጎቹን መሠረታዊ ባህሪይ ነው፡፡ የአንድ ሕግ መሠረታዊ ባህሪይ የሚባለው ሕግ አውጭው ሕጉን ካወጣበት አላማ አንጻር ሕጉ በዋናነት ሊመራው (regeulate) ሊያደርገው የፈለገው ጉዳይ ነው፡፡

የህጉን መሠረታዊ ባህሪይ ማወቅ ሕጉ የሚገኝበትን ክፍል እና ንዑስ ክፍል ለማወቅና ተፈላጊውን ሕግ በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል፡፡

ይህንን ሀሳብ በምሳሌ ለማስረዳት ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ስለሚላክ ዝባድ የወጣውን ደንብ ማየት ይቻላል፡፡ ይህ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ የሚገኘው በተጠቃለሉ የፌዴራል ሕጎች ቅጽ 7ሀ ክፍል 19 ንዑስ ክፍል 15 ሐ ገጽ....... ስለ ልዩ ልዩ የንግድ ሕጎች በሚለው ርዕስ ተራ ቁጥር 1 ላይ ነው፡፡

ዝባድ ጥሪና ከሚባል እንስሳ የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብት በመሆኑ በመጀመሪያ እይታ ይህ ሕግ ሊገኝ የሚችለው ስለ ግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ልማት በሚያወጣው ክፍል 16 ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ሕጉ በመሠረታዊነት ሊመራ እና ሊያስተዳድር የፈለገው የዝባድን አጠባበቅ በተመለከተ ሳይሆን የዝበድን የውጭ ንግድ ጉዳይን በተመለከተ ስለሆነ ሕጉ በክፍል 16 ከሚመደብ ይልቅ በክፍል 18



www.chilot.me

ስር ቢመደብ ይሻላል በሚል በክፍል 18 በንግድና ኢንዱስትሪ ስር እንዲመደብ ተደርጓል፡፡

አንድ ክፍል ወይም ንዑስ ክፍል በዚያ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ሕጎች የሚወክል ስያሜ ሊኖረው አይችልም፡፡ ቢሆንም የክፍሉ ወይም ንዑስ ክፍሉ ስያሜ በዚያ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን ሕጎች መሠረታዊ እና የጋራ ጠባይ እንዲወክል ተደርጎ ተሰይሟል፡፡

በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ የሚገኙን በሥራ ላይ ያለን ሕግ ማግኛው ሌላ ዜዴ በቅጽ 1 ላይ የሚገኘውን የሕጎች አጠቃላይ ዝርዝር ማውጫ መመልከት ነው፡፡ በአጠቃላይ የሕጎችን ዝርዝር ማውጫ ላይ እያንዳንዱ ሕግ በሥራ ላይ ያለ፣ የተሻረ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ከስራ ውጭ መሆኑን አለመሆኑ እና ሕጉ የሚገኝበት የተጠቃለሉ ሕጎች ቅጽ እና ገጽ ተመልክቷል፡፡ የነጋሪት ጋዜጣውን አጭር ርዕስ የሚያውቅ ሰው ይህንን አጠቃላይ የሕጎች ዝርዝር በማየት ከዚህ በላይ የተገለጹት ዘዴዎች የፌዴራል ሕጎች ተጠቃልለው ሕትመት በገቡበት ጊዜ እያንዳንዱ የፌዴራል ሕግ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ የሚረዱ ቢሆንም የተጠቃለሉ ሕጎች ታትመው ከወጡ በኋላ ሕጎቹን ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ በየጊዜው የሚወጡ የተጠቃለሉ ሕጎችን ማሟያ ወይም ኦፊሴላዊውን ነጋሪት ጋዜጣ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

አንዳንድ ሁኔታዎች በፍጥነት የሚለዋወጡ በመሆናቸው የሁኔታዎች መለወጥ የነባር ሕግን መሻሻል ወይም አዲስ ህግን መደንገግ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በመሆኑም የተጠቃለሉ ሕጎች ታትመው በወጡ ጊዜ በሥራ ላይ ነበር የተባለው ሕግ ተጠቃሚው ሕጉን በሚያይበት ጊዜም በእርግጥም ሕጉ በሥራ ላይ መሆን አለመሆኑን ማጣራት ያስፈልገዋል፡፡ (በስራ ላይ ያለው ተፈላጊ ሕግ የሚገኝበትን ቅጽና ገጽ በቀላሉ ለማግኘት ይችላል፡፡)

## 9. <u>የአጠቃላይ ሕጎች ዝርዝር ማውጫ</u>

ተጠቃሚው በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን በቀላሉ ማግኘት እንዲችል በተጠቃለሉ ሕጎች የመጨረሻ ቅጽ በሆነው በቅጽ 7 መጨረሻ ላይ አጠቃላይ የሕጎች ዝርዝር ማውጫ ተዘጋጅቷል፡፡

የሕጎች ዝርዝር ማውጫ መሰረታዊ አላማ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎች በቀላሉ ተፈልገው የሚገኙበትን ዜዴ መቀየስ ቢሆንም ዝርዝሩ የኢትዮጵያን የሕግ አወጣጥ ታሪክ ማጥናት ለሚፈልጉ አጥኚዎችም መነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ አጠቃላይ የሕጎችን ዝርዝር ማውጫ ማዘጋጀት፤ አድካሚ ሥራ ቢሆንም በዘመናዊት የኢትዮጵያ ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ መታተም ከጀመሩበት ከ1934 ዓ/ም ጀምሮ የወጡትን ሕጎች ሙሉ ዝርዝር ማቅረቡ እያንዳንዱ ሕግ ያለበትን ደረጃ በሚገባ ለመለየት የሚያስችልና የሀገሪቷ የህግ አወጣጥ ስርዓት ታሪክ ምን ይመስል እንደነበረ ለመረዳት እንዲቻል በማደረግ በዘርፉ የሚደረጉ ጥናቶችን ለማበረታታትም ቁልፍ ሚና የሚጫወት በመሆኑ ዝርዝሩ ተዘጋጅቷል፡፡

የሕጎቹ ዝርዝር ማውጫ የተዘጋጀው ሕጎች የወጡበትን ዘመን ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ ሲሆን ሕጎቹ በየአይነታቸው ተከፋፍለው ተሰናድተዋል፡፡ ሕጎቹ ሕግ አውጭው በአፊሴላዊው ነጋሪት ጋዜጣ ላይ በተገለጹበት እና በተጠቃለሉ ሕጎች አጠቃቀስ ፎርም ላይ በተገለጸው አኳኋን ተመልክተዋል፡፡

በሕጉ ስያሜ አንጻር የተጠቃለሉ ሕጎች ታትመው በወጡበት ጊዜ ሕጉ ያለበትን ደረጃ ሕጉ ተሽሮ ወይም ተሻሽሎ ከሆነ በምን አግባብ እንደተሻረ ወይም እንደተሻሻለ እና ሻሪው ወይም አሻሻዩ ሕግ ማን እንደሆነ የሚገልጽ መረጃ ተሰጥቷል፡፡

አንዳንድ ሕጎች በሕጎች ላይ በስራ ላይ ያሉ ያልተሻሻሉ ባህሪይ የተነሳ ይዞታቸውን በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ ለማግኘት አይቻልም፡፡

በአለም አቀፍ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጆች የጸደቁ ስምምነቶች፣ የበጀት ሕጎች፣ ኮዶች ወይም የተዋሃዱ ሕጎች) እና በ52/60 (1985) ደ-122 የኢትዮጵያ ሕግ አካል የተደረገው ስምምነት ሙሉ ይዘት በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ አልተካተቱም፡፡

## 10. <u>የአጠቃቀስ ፎርሞች</u>

በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ የሚገኙት ሕጎች የተጠቀሱት (የተገለጹት) ነጋሪት ጋዜጣ ላይ በተመለከቱበት አግባብ ነው፡፡



www.chilot.me

ይኸውም እያንዳንዱ ነጋሪት ጋዜጣ ከሌሎች ነጋሪት ጋዜጣዎች ለመለየት እንዲያስችል ተብሎ በኢፌሴል ነጋሪት ጋዜጣ ላይ የተጻፈው የነጋሪት ጋዜጣው ዓመት፣ የአመቱን የነጋሪት ጋዜጣ እትም ቁጥር፣ ሕጉ የወጣበት ዓመተ ምህረት የሕጉ አይነት ስም እና የተጠቀሰው ሕግ አይነት ተከታታይ ቁጥር ሕግ አውጪው አፌሴላዊውን ነጋሪት ጋዜጣ ባመላከተበት አግባብ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ በሕጎቹ አናት፣ የግርጌ ማስታወሻም ሆነ በሌሎች ስፍራዎች ይኸው የአጠቃቀስ ፎርም በወጥነት በጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የሕጎችን አጠቃቀስ በቀላሉ ለመረዳት እንዲቻል የሁለት አይነት ሕጎች አጠቃቀስ በምሳሌነት ቀርበዋል፡፡

ሀ. <u>10/2 (1996) አ.376 ስለ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ</u>

- ከህዝባሩ በፊት የሚገኘው "10" ቁጥር የሚያሳየው አዋጁ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት በወጣ በአስረኛው አመት የወጣ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡
- ከህዝባሩ በኋላ የሚገኘው "2" ቁጥር የሚያሳየው ደግሞ አዋጅ በ1996 ዓ/ም ከወጡት አዋጆች መካከል በሁለተኛነት የወጣ መሆኑን ነው፡፡
- በቅንፍ ውስጥ የሚገኘው "1996" አዋጁ በ1996 ዓመተ ምህረት መውጣቱን ያመለክታል፡፡ ሕጉ የወጣበትን ዘመን አስመልክቶ የአዋጁ የአማረኛ ቅጂ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የተጻፈ ነው፡፡
- ከቅንፉ ቀጥሎ የሚገኘው ፊደል "አ" (ምህጻረ ቃል) የሕጉ አይነት አዋጅ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ የተካተቱት ሕጎች የወጡት በተለያዩ ዘመነ መንግስት ነው፡፡ ሕጎች በኢትዮጵያ ንገሰ ነገስት መንግስት፣ በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት፣ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስትና፣ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስትና፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የወጡ ናቸው፡፡ እንደ መንግስታቱ የአስተዳር እርከን ባህሪይ የሕጎች አውጪ ባለሥልጣንና የሕጎቹ አይነት ይለያያል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ውጭ ያሉ አዋጆች በሙሉ የሚወጡት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን ምርጫን በተመለከተ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ



www.chilot.me

ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የምርጫ ቦርድ ከሚወጡት ደንቦ ውጭ ያሉት ደንቦች በሙሉ የሚወጡት በኢፌድሪ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡ በተጠቃለሉ ሕጎች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ምህጻረ ቃላት (ፊደላት) እንደ ሕጉ አይነት ስም ይለያያል፡፡

- የህጉ አይነት አዋጅ ከሆነ "አ"
- የህጉ አይነት ደንብ ከሆነ "ደ"
- የሕጉ አይነት ድንጋጌ ከሆነ "ድ"
- የህጉ አይነት የመንግስት ማስታወቂያ ከሆነ "ማስ"
- የሕጉ አይነት የህግ ክፍል ማስታወቂያ ከሆነ "ሕ" የህጉ ስም ምህጻረ ቃል በመሆን ያገለግላል፡፡
- ከዚህ ቀድሞ የወጣን ሕግ ለማረም የወጣ ማረሚያ "ማረ" በሚል ምህጻር ቃል ተፈጽፎአል፡፡

11.<u>የገጾች ቁጥር አሰጣጥ</u>

ከላይ እንደተገለጸው ዘመናዊው የኢትዮጵያ የሕግ አወጣጥ ስርዓት ከተጀመረበት ከ1934 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 2009 ዓ/ም ድረስ ያሉት በሥራ ላይ ያሉ ሕጎች ተጠቃልለዋል፡፡

ለአጠቃቀም ምቹነት እና ለአያያዝ ሲባል የተጠቃለሉት ሕጎች በሰባት ቅጽ (ቮልዩም) ተከፋፈለው እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡

በእያንዳንዱ ቅጽ ላይ ያለው ገጽ የአርበኛው ቁጥር የተሰጠው ሲሆን የቅጽ የመጀመሪያ ገጽ ገጽ 1 የተባለ ሲሆን የቅጽ የመጨረሻ ገጽ ለዘያ ቅጽ የመመጨረሻው ገጽ ቁጥር ተሰጥቶታል፡፡

በ1965 ዓ/ም በተዘጋጁት የተጠቃለሉ ሕጎች መጻፍት ላይ ከጥቅም ላይ የዋለው የገጽ አሰጣጥ ሥርዓት ተጠቃሚውን የሚያደናግር በመሆኑ እንዲቀር ተደርጓል፡፡

በስተመጨረሻም ይህ የህግ ማጠቃለል ስራ በከፍተኛ ጥንቃቄ የተዘጋጀ ቢሆንም በክርክር ወቅትም ሆነ በክስ እና መልስ ዝግጅት ላይ በተጠቃለሉ የኢትዮጵያ ህጎች ውስጥ የተካተተውን ህግ እንጂ የህግ ማጠቃለል ስራውን ጠቅሶ ክርክር ማድረግ ወይም የህግ ጉዳይን ማስረዳት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ በ2009 ዓ/ም በተጠቃለለው የኢትዮጵያ ህጎች ቅጽ 6 ክፍል 15 በሚል ክርክርን ማካሄድ አይቻልም፡፡